# የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ!

(ከአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)
Email: ahayder2000@gmail.com

በፋክት መጽሔት ቁጥር 29 እትም ላይ "አስተያየት በሦስት ጉዳዮች ላይ" በሚል ርእስ አንድ ጽሁፍ አቅርቤ ነበር። አበበ አካሉ ክብረት የተባሉ ግለሰብ ለዚያ ጽሑፌ በዚያው በፋክት መጽሔት ቁጥር 31 እትም ላይ መልስ ሰጥተው ነበር። እኔም የመልስ መልስ አዘጋጅቼ ለመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል በኢሜይል ልኬ ነበር። መድረሱንም አረጋግጫለሁ። ይሁን እንጂ የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል ጽሁፉ እንደማይታተም ገልጸልኛል። እኔን ካሰደበ በኂላ መልስ የመስጠት መብቴን ከልክሎኛል። እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ የተሳሳተና የሀገሪቱን የፕሬስ ሕግ (The Right to Replay) ያላከበረ መሆኑን ባውቅም፤ ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል ጋር የሚኖረኝን ቀጣይ ግንኙነት ላለማበላሸት በማሰብ እሰጥ አገባውን ለጊዜው መተውን መርጫለሁ።

እዚህ ላይ የመጽሔቱ አዘጋጆች መገንዘብ ያለባቸው፤ ይሄ መድረክ የተፈጠረውና እነሱ ዛሬ የሚፈልጉትን የሚገፉበትና የሚፈልጉትን የሚያስተናግዱበት መጽሔት ማቋቋም የቻሉት ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በከፈሉት መስዋእትነት በመሆኑ፤ እነሱ ገንዘባቸውን ኢንቨስት ቢያደርጉበትም መጽሔቱ የሕዝብ መድረክ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል። እነሱም ቢሆኑ "ኢህአዴግ አፋኝ ነው፣ አፋኝ የፕሬስ ሕግ ያወጣል፣ ጋዜጠኞችን ያስራል ..." ምናምን እያሉ በኢሕአዴግ ላይ ጣታቸውን ከመቀሰራቸው በፊት ባለቻቸው ስልጣን ተጠቅመው እየፈጸሙት ያለውን ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ አፈና ማቆም ይኖርባቸዋል። ይህንን ካልኩ በኂላ በመጽሔቱ ላይ አቶ አበበ አካሉ ወዳነሱት ሃሳብ ላምራ።

በፋክት መጽሔት ቁጥር 29 እትም ባቀረብኩት ጽሁፍ ላይ አበበ አካሉ ክብረት የተባሉ ጸሐፊ በቅጽ 2 ቁጥር 31 የመጽሔቱ እትም ላይ አስተያየታቸውን አቅርበዋል። የእኔ ጽሁፍ መነሻ ያደረጋቸው የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶች የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሣለኝ እና አቶ አስራት አብርሃ እያሉ፤ አቶ አበበ እነሱን ተክተው መልስ መስጠታቸው "የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ" የሚያሰኛቸው መሆኑን እገነዘባለሁ። ይሁን እንጂ፣ እሳቸውም ቢሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ወደ 'ክርክሩ ሜዳ' መምጣታቸው ክፋት ስለሌለው በአንዳንድ ያልጠሩ ጉዳዮች ላይ እሳቸው ካቀረቡት ሃሳብ በመነሳት ያለኝን ምላሽ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ከሁሉ በፊት ግን አንድ ነገር ለማስቀደም ወደድሁ። የእኔ ፍላጎትም ሆነ እምነት የአዲሱ ትውልድ አባላት ከታላላቆቻችን በተለየና በተሻለ ሁኔታ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ክርክር በማድረግ አንድነታችንን እና ልዩነታችንን አንጥሮ የማውጣት ባህል ማዳበር ነው። እነዚህም ክርክሮቻችን በሃሳብ (Issues) ላይ ያተኮሩ፣ የጸሐፊውን ማንነትም ሆነ ምንነት የማያጣቅሱና ሰብእናውን የማይነኩ፣ በተነሳው ርእሰ ጉዳይ ላይ እንጂ በጎንዮሽ ጉዳዮች (side issue) ላይ የማያተኩሩ መሆን ይኖርባቸዋል። በበኩሌ በምናደርገው ክርክር መሳደብም መሰደብም አልፈልግም።

ስልጣኔ ማለት ንፁህ የለንደን ሱፍ መልበስ፣ የጣሊያን ጫማ መደንቀር አሊያም የፈረንሳይ ሽሚዝና ከረቫት አንገት ላይ ማበት አደለም። ለእኔ እንደሚገባኝ ስልጣኔ ማለት በስድብ፣ በአግቦ በአሽሙርና በቅኔ መራቀቅ ማለትም አደለም። በዚህኛው መንገድ ረዥም ርቀት

መጥተንበታል። ከቂምና ከቁርሾ በስተቀር ያተረፍነው ነገር የለም። ይሁን እንጂ፣ አቶ አበበ ይህንን አጠቃላይ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባለማስገባታቸው ያቀረቡት ጽሁፍ እኔ ባነሳሁዋቸው ሃሳቦች ላይ ብቻ ያተኮረ አልነበረም። ወደ ጎን እየሄዱ አንዳንድ ነገሮችን ነካክተዋል። ፍፁም በማያውቁት ጉዳይ ላይም ጽፈዋል። አልፎ አልፎ ስድብ ጭምር ሰንዝረዋል። ሁሉንም እያነሳሁ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ።

አቶ አበበ ጽሁፋቸውን "ሀ" ብለው የሚጀምሩት "የቀድሞ የፓርላማ አባል የሚል ጭንብል" አጥልቄ በየጋዜጣውና በየመጽሔቱ ላይ ብቅ ብቅ በማለት ሙግት መጀመሬን በማንሳት ነው። አቶ አበበ እኔ ያነሳኂቸውን ሃሳቦች እየጠቀሱ መከራከር ሲችሉ "የቀድሞ የፓርላማ አባል የሚል ጭንብል" የሚለውን ተቀጽላ መደንቀር ለምን አስፈለጋቸው? የፓርላማ አባል እንደነበርኩ ከተጠራጠሩ የሚያውቁትን ነገር ጠቅሰው መከራከሪያ ማቅረብ አንድ ነገር ነው። '**ጭንብል**' ምናምን ማለት የሚያስፈልግ አይመስለኝም - ያጠለቅኩት አንዳችም ነገር የለምና! ባደጉትና በሰለጠኑትም ሀገራት ፈረንጆቹ የቀድሞ የፓርላማ አባላት "Ex-MP" እያሉ ይጠቀማሉ። የኔውም ከዚያ የተኮረጀ ነው።

በነገራችን ላይ በ1997 ዓ.ም በተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ እኔ የተመረጥኩት አዲስ አበባ ላይ በተደረገ የቴሌቪዥን ክርክርና ጩኸት አልነበረም። (በዚያ ወቅት እኔ በተወዳደርኩበት ወረዳ፣ በመርሣ ከተማ፣ ሦስት ቴሌቪዥኖች ብቻ እንደነበሩ አስታውሳለሁ) ከአምስት መቶ ኪሎ ሜትር ያላነሰ መንገድ በእግሬ ተጉዤ፣ ተራራ ወጥቼ፣ ቁልቁለት ወርጄ፣ ጨካ አቋርጬ፣ በውሃ ሙላት በጎርፍ ከመወሰድ አምልጬ፣ ከአፋር ድንበር እስከ ወልዲያ ጫፍ፣ በወዲህም ከወረባቦ እስከ አምባሰል አፋፍ ድረስ፣ ለ75 ቀናት፣ በ33 የገጠር የመንደሮች ተንከራትቼ ባደረግኩት ቅስቀሳ ነበር የተመረጥኩት። (አንዳንዱ እንቅስቃሴየ በፊልም የተቀረጸ ነው) እናም ያንን የምክር ቤት ዘመን ማስታወስ ያንሰኝ እንደሆነ እንጂ የሚበዛብኝና የሚያስወቅሰኝ መስሎ አይታየኝም። አቶ አበበም ***የጭንብሉን*** ነገር ይተውትና ሀቁን በዚህ መልኩ ቢረዱት መልካም ነው።

"... በአቶ ተመስገን ዘውዴ ሕይወትና የትግል ተሞክሮ ዙሪያ... [በተ]ዘጋጀው መጽሐፍ ዙሪያ ተንተርሰው ብዕራቸውን በተከታታይ ሲያነሱ ተመልክቼ ተገረምኩኝ" ይላሉ አቶ አበበ፣ ጽሑፋቸው መግቢያ ላይ። ምኑ ነው ያስገረምዎት አቶ አበበ? ሰው መልካም ስሙን አላስጎድፍም፣ መብቴን አላስነካም ማለቱ ያስገርማል እንዴ? ለጻፍኩት ጽሑፍ ምንም መልስ የሌላቸው አቶ ተመስገን ዝምታን ሲመርጡ እርስዎ 'ለአቶ ተመስገን መልስ ሰጠህ' ብለው መጻፍዎ ነው ይልቅስ የሚያስገርመው። ወዳጄ! መገረም የነበረብዎት በውሸት ስሜ ጠፍቶ ዝም ብል ነበር።

አቶ አበበ ይህንንም ብለው ቢያቆሙ ጥሩ ነበር። ይቀጥሉና "ለዚህ ያነሳሳቸው የእውነት ቁጭት ሳይሆን በመጽሐፉ ውስጥ የእሳቸው ስም በመጥፎ ጎኑ መነካቱ አንገብግቧቸው ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም" የሚል ሃሳብ ያክሉበታል። አቶ አበበ! እኔ ለአቶ ተመስገን መልስ ለሰጠሁ እርስዎን ምን አናደደዎት? ይሄ ታዲያ "የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ!" አያሰኝም? እንዲያው ለነገሩ ጽሁፉን የጻፍኩት ለእውነት በመቆጨት ይሁን አይሁን በምን አወቁ? ስሜ በውሸት መነሳቱን ለመከላከል መጻፍ በራሱ "ለእውነት መቆርቆር" አይሆንም? ወይስ የአንተ ስም በከንቱ መጥፋት አለበት እያሉ ነው አቶ አበበ?

በሌላ በኩል፣ ሰው ለራሱ ያልተቆረቆረ ታዲያ ለማን ሊቆረቆር ኖሯል? ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አቶ አበበ ጽሁፌን በቅን ልቡና ካዩት መነሻየም መድረሻየም ለእውነት መቆርቆር መሆኑን ይረዱታል። በአቶ ተመስገን ላይ ያነሳሁት ሀሳብ ውሸት ነው የሚሉ ከሆነ አንድ፣ ሁለት

ብለው በመጥቀስ እሱን ይተቹ፡፡ ካለበለዚያ የእኔን የውስጥ ፍላጎት (Motive) ፍለጋ መኳተኑ ትርፉ ድካም ነው፡፡ አቶ አበበ ራሳቸው ለሚወዱት ሰው ሳይሆን፣ ለእውነት የመቆርቆር ጠንካራ አቋም ቢኖራቸው ኖሮ የእኔ ስም በውሸት መቆሸሹ ያንገበግባቸው ነበር እንጂ መልስ መስጠቴ አይገርማቸውም ነበር፡፡ ነው ወይስ የአንተ ስም በውሸትም ቢሆን መነሳቱ ተገቢ ስለሆነ መልስ መስጠት አልነበረብህም እያሉኝ ነው? ለምን አቶ አበበ? እስላም ስለሆንኩ?

አዎ! እንዲህ ያለ ጥያቄ ያቀረብኩት የአቶ አበበን የውስጥ ፍላጎት (ሞቲቭ) እንዲህ ሳይሆን አይቀርም ብዬ በራሴ መንገድ ተርጉሜ ነው፡፡ ይህን ያደረግኩት ግን የሰውን የውስጥ ፍላጎት (ሞቲቭ) እንዲህ ይሆናል ብሎ ማንበብ ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ለአቶ አበበም ሆነ ለአንባቢ ለማሳየት ነው እንጂ እውነትም አቶ አበበ "እስላም ስለሆንኩ" እንደዚያ ዓይነት አስተያየት ሊኖራቸው እንደማይችል አስባለሁ፡፡ ከበስተጀርባ አለ የሚሉትን የሰውን 'ፍላጎት ማንበብ' ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ አዩት አቶ አበበ? እኔ የምጠላው እንዲህ ያለውን መንገድ ነው፡፡ እርስዎ በሃሳብ ላይ ብቻ ትኩረት ቢያደርጉ ኖሮ እኔም እንዲህ ያለ ጭቃ ረገጣ ውስጥ አልገባም ነበር፡፡ ለማንኛውም ቅን ልቦና ይስጥዎት!

በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ያቀረብኳቸውን (አቶ አበበ የተንሸዋረሩ ያሏቸውን) ሃሳቦች አንድ በአንድ እየጠቀሱ መተቸትን ያልመረጡት አቶ አበበ "አቶ አብዱራህማን እስከ ዛሬ የትኛው **ዛጎል** ውስጥ ተደብቀው እንደከረሙ ሳይታወቅ ሰሞነኛ ለመሆን ብዕር አነሱ፡፡ ችግሩ አላዋቂ ሳሚ … እንዲሉ ሆነ እንጂ" በማለት፣ ፋክት መጽሔት ላይ 'በድፍረት' ጽፌ ትዝብት ላይ እንደወደቅኩ ይነግሩኛል፡፡ ይህንን አባባል ሳነብ አቶ አበበ ስህተቴን ጎልጉለው በማውጣት የእርሳቸውን ታላቅነትና "አዋቂነት" ሊያሳዩኝ ነው ብየ ነበር፡፡ ዳሩ ምን ያደርጋል ጽሁፋቸው ለእኔ ያላቸውን ጥላቻ ከማንጸባረቅ ውጪ ሊቅነታቸውን ሊያሳየኝ ከቶ አልቻለም፡፡

አቶ አበበ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ሰው **ዛጎል** ውስጥ ይገባል እንዴ? የእርስዎን ባላውቅም ለማንኛውም እኔ ዛጎል ውስጥ ቀርቶ ምንም ነገር ውስጥ እንድደበቅ ግድ የሚለኝ ሀጢያትም ሆነ ነውር ስለሌለኝ ተደብቄ አላውቅም፡፡ ወደፊትም አልደበቅም፡፡ መጻፍንም በተመለከተ፣ ሰሞነኛ ጉዳይ አደለም፡፡ ምናልባት የእርስዎ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን የማንበቡ ሁኔታ ሰሞነኛ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እኔማ ከፖለቲካው ብወጣም አቅም በፈቀደ መጠን በሀገሬ ጉዳይ ላይ ያለኝን ስሜት ገልጬ እጽፋለሁ፡፡ ወደፊትም እንዳስፈላጊነቱ እሞካክራለሁ፡፡ እድሜዬ ገና በአስራዎቹ አጋማሽ ላይ እያለ ጀምሬ የጨበጥኩት ብዕር አፎቱ ውስጥ የሚገባው እኔ መሬት ውስጥ ስገባ እንደሚሆን አስባለሁ፡፡

አቶ አበበ ወዳነሱት ሌላ የጎንዮሽ ጉዳይ ላምራ፡፡ "እብሪቅ" የሚለውን ቃል በጽሁፌ መጠቀሜን በማንሳት "የእስልምና እምነት ተከታዮች… ውሃ የሚይዙበትን ክቡር ዕቃ" እንዳራከስኩና ይህም የእምነቱን አስተምህሮ "መገዳደር" እንደሆነ በመግለጽ የእምነቱ ተከታዮች "እንዲነሱብኝ" ይቀሰቅሳሉ አቶ አበበ፡፡ የእምነቱን ቀኖና (ዶግማ) "ጠንቅቆ አለመረዳት ነው" በማለት ከቶም እስልምናን ሊያስተምሩኝ 'ከጳጳሱ ቄሱ' ሆነው ብቀ ይላሉ አቶ አበበ፡፡ መቼስ አንዳንድ ጊዜ ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተምራለሁ ብትል ክፋት የለው! ችግር የሚፈጠረው ምጥ ምን እንደሆነ እውቀት የሌላት ልጅ ስለምጥ አስተምራለሁ ብላ የተነሳች እንደሆነ ነው!!!

በመጀመሪያ ደረጃ ሙስሊሞች ማንም ሰው ተነስቶ ስለጻፈ ስሜታዊ እርምጃ ይወስዳሉ ብለው ጠብቀው ከሆነ ተሳስተዋል፡፡ እንዲህ ያለው "የመሐል አገር ፖለቲካ" ጊዜው ያለፈበት አይመስልዎትም አቶ አበበ? በሁለተኛ ደረጃ አቶ አበበ ማወቅ ያለብዎት በእስልምና አስተምህሮ ውስጥ "ዶግማ፣ ቀኖና፣ ምንጣፍ፣ እብሪቅ፣ የክብር እቃ፣…" ምናምን የሚባል ከእምነቱ ጋር ተያይዞ የሚመለክ ነገር የሌለ መሆኑን ነው፡፡ እናም እብሪቅን በቀልድ መልክ ማንሳቴ ያን

ያህል የሚካበድ ነገር አደለም፡፡ ብፈልግ “እብሪቶች ሁሉ ይቃጠሉ ወይም በግራካሦ በኩል ያቋርጡ” ብዬ መጻፍ እችላለሁ፡፡ የእብሪቅ ሚና ውሃ ከመያዝ የዘለለ አደለም፡፡ በነገራችን ላይ ከእብሪቅ በፊት የዱሮዎቹ ሼህዎች በቅል (በጡሌ) ይጠቀሙ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በላስቲክም ይጠቀማሉ፡፡

አቶ አበበ “ይህንን ተግሳጽ ለእምነቱ ምሁራን ልተወውና…” ያሉት በርግጥም ለእስልምና ሃይማኖት በመቆርቆር ሳይሆን እኔን ያሳጣሁ መስሏቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጸሐፊው እኔን ወጥመድ ውስጥ እከታለሁ ሲሉ፤ እስልምናን ከቁሳቁስ ጋር አያይዘው በማቅረብ ራሳቸውን ወጥመድ ውስጥ የከተቱ ይመስለኛል፡፡ ከሆነ አይቀር “አላዋቂ ሳሚ…” ሊሰኝ የሚችለው እንዲህ ያለው አካሄድ ይመስለኛል፡፡

አቶ አበበ ወደ ሃሳብ ክርክር በመሸጋገር ያነሱት ጉዳይ ሻምበል ጉታ ዲንቃ ከአቶ ኃ/ማሪያም ጋር ለማንዴላ ቀብር ወደ ደቡብ አፍሪካ ቢሄዱ “ኢትዮጵያ ለአፓርታይድ መፍረስ” ያደረገቺው አስተዋጽዖ ይንጸባረቃል የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት **አንደኛ፡-** ጉዳዩ አንዴ አልፏል፡፡ ይሁን ቢባል እንኳ ሊሆን አይችልም፡፡ እናም በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ክርክር ማድረግ ጉንጭ አልፋ ከመሆን የዘለለ ትርጉምም ፋይዳም የለውም፡፡ **ሁለተኛ፡-** አቶ ኃ/ማሪያም የሄዱት በቀብር ሥነ-ስርዓት ላይ ለመገኘት ነው ወይስ ኢትዮጵያ ለአፓርታይድ መፍረስ ያደረገቺውን አስተዋጽዖ ለማስረዳት? **ሦስተኛ፡-** ለቀብር ሥነ- ስርዓቱ በሚሊዮን የሚቆጠር የዓለም ሕዝብ በተሰበሰበበት ሁኔታ እንኳን የሻምበል ጉታ መምጣት በደቡብ አፍሪካውያን ሊታወቅና የታሪክ ትንታኔ ሊደረግበት ቀርቶ የአቶ ኃ/ማሪያም በስፍራው መገኘት ራሱ ልብ ሊባል የሚችል መስሎ አይታየኝም፡፡

አቶ አበበ “ሻምበል ጉታ ከአቶ ኃ/ማሪያም ጋር በቀብር ሥነ-ስርዓቱ ላይ ቢገኙ ‘ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይናገር የነበረ’ እንዲሉ ኢትዮጵያ ለደቡብ አፍሪካውያን ነፃነት ከማንዴላ ጎን መሰለፏን መመስከር” ይችላሉ የሚሉትስ እንዴት ሆኖ ነው? ሀዘኑ ቀርቶ ሻምበል ጉታ ኢትዮጵያ ለፀረ-አፓርታይድ ትግል ስላደረገቺው አስተዋጽዖ ንግግር ሊያደርጉ ማለት ነው? ለመሆኑ አቶ ኃ/ማሪያም ራሳቸው በዚያ ሥነ-ስርዓት ላይ ንግግር ማድረግ ችለዋል? ተናግረውም ከሆነ የአፍሪካ ህብረት የወቅቱ ሊቀ መንበር በመሆናቸው ነው እንጂ በኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው ሊሆን እንደማይችል እገምታለሁ፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር በአጽንኦት እንዲታይ እሻለሁ፡፡ ይኸውም፤ ሻምበል ጉታም ሆኑ ሀገራችን ለፀረ-አፓርታይድ ትግል አስተዋጽዖ ማድረጋቸው ላይ ልዩነት የለኝም፡፡ የኔ ጥያቄ፤ ይሄ የአገራችን አስተዋጽዖ በደቡብ አፍሪካውያን አይታወቅም ወይ? የሚል ነው፡፡ በበኩሌ ቢያንስ ቢያንስ በፖለቲከኞቹና በምሁራን አካባቢ ይታወቃል ባይ ነኝ፡፡ ባይታወቅስ? ይህንን ለማሳወቅ ወደ ደቡብ አፍሪካ መሄድ ያለብን በማንዴላ የቀብር ሥነ-ስርዓት እለት ነው? ይህንንስ ለማሳወቅ እዚያ ድረስ መሄድ አለብን?

‘ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም’ እንዲሉ የሀገራችንም ሆነ እንደ ሻምበል ጉታ ያሉ ኢትዮጵያውያን የፀረ-አፓርታይድ ትግል አስተዋጽዖ በደቡብ አፍሪካውያን ዘንድ እንዲታወቅ ከፈለግን እዚሁ አዲስ አበባ፤ ደቡብ አፍሪካ ኤምባሲ ውስጥ የማንዴላ የሀዘን መታሰቢያ ሥነ-ስርዓት በማድረግ ሁኔታውን በቪዲዮ ቀርፆ ማሰራጨት አይሻልም ወይ? አማራጭ መንገዶችን መጠቀም ሲቻል፤ ‘ሻምበል ጉታ ከአቶ ኃ/ማሪም ጋር መሄድ አለባቸው፣ የለባቸውም’ የሚል ክርክር አንስቶ ድርቅ ማለት ሊገባኝ አይችልም፡፡

“ስለፕሮቶኮል አጠባበቅ ለፕሮፌሰሩ ማስተማርም የቃጣቸው ይመስለኛል” ይላሉ አቶ አበበ። ከዚህ አባባል **አንደኛ፡-** ስለፕሮቶኮል ያነሳሁት ሃሳብ ስህተት መሆኑን በማስረዳት ሃሳቤን ‘ፉርሽ’ ማድረግ አለመቻላቸውን፣ **ሁለተኛ፡-** “ፕሮቶኮል” የተሰኘውን ጽንሰ ሐሳብ በተመለከተ አቶ አበበ የጠራ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን፣ **ሦስተኛ፡-** “ማስተማር ቃጣቸው” የሚለው አገላለጽ ‘ፕሮፌሰር መስፍንን ያህል ትልቅ ምሁር እንደ አንተ ያለ ተራ ሰው ስለ ፕሮቶኮል ሊያስተምር አይችልም’ የሚል መንፈስ ያለው መከራከሪያ የቀረበ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ።

በመጀመሪያ ደረጃ ፕሮቶኮል ተራ ነገር አለመሆኑ መታወቅ አለበት። ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ ትልቅ ትርጉም አለው። አፄ ቴዎድሮስ ከአማታቸው ከራስ ዓሊ ቤት ለእርሳቸው የስልጣን ደረጃ የማይመጥን (ፕሮቶኮል ያላሟላ) የሥጋ ዓይነት (ብልት) ስለተላከላቸው ባደረባቸው ብስጭት ተነሳስተው ባይዋጉ ኖሮ ለንጉሠ-ነገስትነት አይበቁም ነበር። በሌላ በኩል፤ ፕሮፌሰር መስፍን የሊቅነት ማዕረጉን ያገኙት በመልክዓ-ምድር (ጂኦግራፊ) እንጂ በሁሉም የእውቀት መስክ አደለም፣ ሊሆንም አይችልም። እናም የፕሮቶኮል ጉዳይ እኔ ለተማርኩት የሙያ መስክ ቀረቤታ ስላለው ካላወቁ ባስተምራቸው ምን ይለኛል? ምንም አይለኝም!

አቶ አበበ! ከሁሉ አስቀድሞ፤ ‘አንዳንድ ሰዎች በአንድ የእውቀት መስክ ሊቅ ስለሆኑ በሁሉም ነገር ሊቅ ናቸው’ ከሚል የአስተሳሰብ እስረኛነት ራስዎን ነፃ ያውጡ። ፕሮፌሰር መስፍን ከእኔ ቀርቶ ከእኔ ልጅ ሊማሩት የሚችሉት ነገር ሊኖር ይችላል። ያን ያህል አይነኬና አይደፈሬ አድርገው አይዩዋቸው። ለነገሩ ፕሮቶኮልን በተመለከተ ፕሮፌሰር መስፍን ከእኔ የሚማሩት ነገር የለም። እኔም በጽሁፌ ላይ “ዘንግተውት ከሆነ ላስታውስዎት” ነው ያልኩት።

ባለፈው ጽሁፌ “የተመስገን አብዮት” በሚል ርእስ ላቀረብኩት ጽሁፍ አቶ አበበ ያቀረቡት ሃሳብ (የጎንዮሽ ሃሳቦችን ሳይጨምር) ጥሩ ነው። በተለይም አብዮት ሊወለድ የሚችለው የተጠራቀመ የህዝብ ብሶትን ተከትሎ እንደሆነ ያቀረቡት ሃሳብ የምቀበለው ነው። እኔ ካቀረብኩት ሃሳብም ጋር የሚጣረስ ሆኖ አልታየኝም። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ግን በዚህ ወቅት በሀገራችን ያን ያህል አብዮት (ሕዝባዊ አመጽ) ሊቀሰቅስ የሚችል ብሶት አለ? የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ነጥቦች ላይ አስተያየት መስጠት እወዳለሁ።

**አንደኛ፡-** አቶ አበበ፤ “22 ዓመታት ሙሉ በ‘አብዮታዊ ዴሞክራሲ’ ስም የሚገዛንን ኢህአዴግ መተቸቱ ቢቀድም” ያሉትን በተመለከተ፣ ለ12 ዓመታት ከእኔ የሚጠበቀውን ሞክሬአለሁ። ከንግዲህ የፖለቲካ አቋም ይዤ መታገል አልፈልግም። በሰው እጅ ሲያዩዋት የምታምረውን አታሞ እየያዛችሁ እስቲ እናንተ ደግሞ ሞክሩት አቶ አበበ! ከንግዲህ የእኔ ሚና መሆን ያለበት፤ የተጀመረው የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት አቅጣጫ እንዳይስትና እስከ አሁን የተከፈለው መስዋእትነት መና እንዳይቀር ገዢውንም ተቃዋሚ ፓርቲዎችንም ማሳሰብ፣ መምከር፣ አቅጣጫ ማሳየት፣ መተቸት፣ ማበረታታት፣… እንጂ የአንዱን ወገን አቋም መደገፍ፣ የሌላውን መንቀፍ አደለም የሚል የግል አቋም አለኝ።

በነገራችን ላይ የአንድ ፓርቲ የፖለቲካ መስመር (ርዕዮተ ዓለም) አብዮታዊ ዴሞክራሲ ተባለ ሊበራል ዴሞክራሲ፣ ሶሻል ዴሞክራሲ ተባለ የቡርዧ ዴሞክራሲ፣… ሁሉም ውግንና አለው። ሁሉም መስመር መብትና ጥቅሙን የሚያስከብርለት የህብረተሰብ ክፍል አለው። ያ ነው የፓርቲዎች ማኅበራዊ መሰረት የሚባለው። እናም አብዮታዊ ዴሞክራሲ መብትና ጥቅማቸውን የሚያስከብርላቸው ወገኖች አሉ። (በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ሃሳብ ይዤ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ)

**ሁለተኛ፡-** የማነሳው ሃሳብ አቶ አበበ "ፀሐፊው ሕገ መንግስቱን በተመለከተም የተዘበራረቀ ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡ የእኔ አረዳድ ተዛብቶ ከሆነ በቅድሚያ ለመታረም ዝግጁ ነኝ" ካሉ በኋላ የእኔን ሃሳብ በሚከተለው ሁኔታ ይጠቅሳሉ፤ "...'አሁን ባለው የኢህአዴግ መስመር የዴሞክራሲ ስርዓት ማረጋገጫ ተቋማት አደረጃጀትም ሆነ የአሰራር ስርዓት አለ ለማለት አያስደፍርም'..." አቶ አበበ! የተዛባው አረዳድዎ አደለም፡፡ የተዛባው እኔ ያልጻፍኩትን አዛብተው መጥቀስዎ ነው፡፡ ሃሳቤ ለትችት አልመችዎት ሲል ሊተቹት የሚፈልጉትን ሃሳብ የእኔ አስመስለው ማቅረብዎ ስህተት ብቻ ሳይሆን ወንጀልም መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ እንደ አንድ የተማረ ሰው ትዝብት ላይ የሚጥልዎትም ነው፡፡

ለማንኛውም እኔ ያልኩት "እንደሚታወቀው አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገ መንግስት በስራ ላይ ከዋለ 19 ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም፤ ሀገሪቱ በዚህ ሕገ መንግስት መሰረት ተሰርታ አልተጠናቀቀችም፡፡ በዚህም ምክንያት ለአንድ ሀገርና ሕዝብ የሚያስፈልጉት የዴሞክራሲ ስርዓት ማረጋገጫ ተቋማት፣ አደረጃጀትም ሆነ የአሰራር ስርዓት በቅጡ አለን ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህ ተጨባጭ እውነታ ባለበት ሁኔታ ሦስተኛ 'አብዮት' እናካሂድ የምንል ከሆነ..." እያለ ይቀጥላል፡፡

ይህ ሃሳብ ከዚያው ቀጥሎ ካቀረብኩት ሃሳብ ጋር ምንም ዓይነት ተቃርኖ የለውም፡፡ አቶ አበበም በደፈናው "የሚጣረሱ ሃሳቦች አሉ" ከማለት ውጪ የሚጣረሱትን ሃሳቦች አንድ በአንድ ነቅሰው አላሳዩም፡፡ ይልቁኑ ወደ ሌላ አቅጣጫ በመሄድ "በወረቀት ላይ ከሰፈረውና በማንኛውም ሰዓት በሕዝብ ይሁንታ ሊሻርና ሊሻሻል የሚችልን ሕገ መንግስት ከዜጎች ልእልና በላይ አግዝፎ ማየት ጤናማ አስተሳሰብ አይመስለኝም" ይላሉ፡፡

ወንድሜ አቶ አበበ! እኔም ሕገ መንግስትን የዜጎች ልእልና መገለጫ አድርጌ እንጂ ከዜጎች ልእልና በላይ አግዝፌ አይቼው አላውቅም፡፡ በጽሁፌም ላይ እንደዚያ ዓይነት ሃሳብ አላንጸባረቅኩም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሕገ መንግስት ማለት የአንድ ሀገር ዜጎች መቶ በመቶ (ሁሉም) የሚስማሙበት ሰነድ ሊሆን አይችልም፡፡ እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ባለ 80 ሚሊዮን ሕዝብ ባለበት ሀገር ቀርቶ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ባላቸው ሀገሮች እንኳ ሁሉም ዜጎች የሚስማሙበት ሕገ መንግስት ሊቀረጽ አይችልም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ሃምሳ አንድ በመቶ (51%) የሚሆኑት ቢስማሙበት፤ አርባ ዘጠኝ በመቶ (49%) የሚሆኑት ይቃወሙታል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዴሞክራሲያዊ የአሰራር መርህ መሰረት ሌላ አማራጭ ስለሌለ የብዙሃኑ (50+1%) ሃሳብ ገዢ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

አሁን ያለንው ሕገ መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚስማማበት እንዳልሆ ይታወቃል፡፡ አቶ አበበ! ነገ እርስዎ የሚደግፉት ፓርቲ አሸናፊ ቢሆን 80 ሚሊዮኑ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ የሚደግፈው ሕገ መንግስት ሊጽፍ አይችልም ብሎ መናገር ነቢይነትን የሚጠይቅ አደለም፡፡ በዚህ ሃሳብ የምንስማማ ከሆነ፤ ያለን አማራጭ አሁን ያለውን ሕገ መንግስት እዚያው ሕገ መንግስቱ ውስጥ በተቀመጠው አግባብ መሰረት እያሻሻልን መቀጠል ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ያደጉትና የሰለጠኑት ሀገሮች የመጡበት የስልጣኔ መንገድም ይሄው ነው፡፡ ለምሣሌ የአሜሪካ ሕገ መንግስት ባለፉት 240 ዓመታት 28 ጊዜ ተሻሽሏል፡፡ እኛም ከዚህ ዓይነቱ አካሄድ ማፈንገጥ የለብንም ነው የምለው፡፡ ከዚህ መንገድ ከወጣን የተጀመረው ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ይፈርሳል፡፡ ይሄ ደግሞ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ይሆናል ነው የምል!

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነገር አሁን ሀገሪቱን እያስተዳደረ ያለው ፓርቲ (ኢህአዴግ) አምባገነን ስለሆነ፣ ፖለቲከኞችን ስለሚያስርና ስለሚያንገላታ፣ የፖለቲካ ምህዳር ስለሚያጠብ፣ ጋዜጠኞችን ስለሚያስር፣ ወዘተ. በእሱ ዘመን የተጻፈውን ሕገ መንግስት ቀዶ

መጣል ጠቃሚ መስሎ አይታየኝም፡፡ እንዲህ የምናደርግ ከሆነ እየቀደዱ የመጣሉ ሂደት ማብቂያ አይኖረውም፡፡ ስለሆነም፤ የመቅደድን ሳይሆን የማሻሻልን አማራጭ እያንገሸገሸንም ቢሆን፣ ጨክን ብለን እንቀበለው ነው የምል!!!

በሌላ በኩል፤ አሁን በተቃውሞው ጎራ የተሰለፈውን ኃይል የመላእክት ስብስብ፣ የዴሞክራሲ ዋስ ጠበቃ አድርገው ባያዩትም መልካም ነው - አቶ አበበ! የኢህአዴግ መሪዎችም ሆኑ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ የፖለቲካ ልሂቃን ከአንድ ወንዝ የተቀዱ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም ባይ ነኝ፡፡ ልዩነታቸው ሥልጣን መያዝና አለመያዝ ብቻ ሆኖ ነው የሚታየኝ፡፡ ወደ ዝርዝር ጉዳይ መግባት ስለማልፈልግ ነው እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ በርካታ ምሣሌዎችን ለማቅረብ አይገደኝም ነበር፡፡

አቶ አበበ በሦስተኛ ደረጃ ባነሳሁት ሃሳብም ላይ አስተያየት አቅርበዋል፡፡ በዚህ ዙሪያ በርካታ ጥሩ ጥሩ ሃሳቦችን አንስተዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተወሰኑ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ታይተውኛል፡፡ በቀዳሚነት የማነሳው አቶ አበበ ውህደት "የኢትዮጵያ ሕዝብ" ፍላጎት መሆኑን መግለጻቸውን በተመለከተ ነው፡፡ አቶ አበበ! "የኢትዮጵያ ሕዝብ" መቼና የት ተሰብስቦ ነው በዚህ ጉዳይ ላይ መክሮ የወሰነው? ወይም አስተያየት የሰጠው? ከሁሉ በፊት "ሕዝቡ እንዲህ ብሎ፣ ሕዝቡ እንደዚያ ብሎ፣… ሕዝቡ… ሕዝቡ…" የሚለው ተለምዷዊ አገላለጽ አሳሳች ነው፡፡ ከመሬት እየተነሳን በሕዝብ ስም መማልና መገዘት ተገቢ መስሎ አይታየኝም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ 80 ሚሊዮን ገደማ ነው፡፡ አዲስ አበባ ላይ ተቀምጠን ባለፍ አገደም የሰማነውን አስተያየት የመላው ህዝብ አስተያየት እንደሆነ አድርጎ ማስቀመጥ ተገቢ አይሆንም፡፡ አቶ አበበ፤ የትኛውን ጥናት (Public opinion poll) አድርገው ነው "ሕዝቡ" ብለው የጻፉት? እንደ ፖለቲከኛ የፖለቲካ ሃሳብ (Political statement) መናገር ስህተት ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይችል እገነዘባለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህንን መናገር ያለባቸው የፖለቲካ መሪዎች ናቸው፡፡ ጋዜጠኛውም፣ ምሁሩም፣ ጸሐፊውም፣ ተራ ዜጋውም፣ ካድሬውም፣… ከመሬት እየተነሳ "ሕዝቡ እንዲህ ብሎ" እያለ የሚናገር ከሆነ አሳሳች ድምዳሜ ላይ መድረስ ይመጣል፡፡ ይሄ ደግሞ በዚች አገር "እውነት" የሚባለውን ነገር አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ ለፖለቲካ ፓርቲዎችም ውድቀት መንስዔ ይሆናል፡፡ የዘጠና ሰባቱን "ቅንጅት" አፈር ከድቤ ያስጋጠው አንዱ ምክንያት እንዲህ ዓይነት ከመጠን በላይ የተለጠጠና ጋዜጦች ሲያጋግሉት የነበረው ግፊት ይመስለኛል፡፡

ሌላው አቶ አበበ ያነሱት አከራካሪ ሃሳብ አውራ ፓርቲን በተመለከተ ዶ/ር ኃይሉ አርአያን በመጥቀስ ያቀረቡት ሃሳብ ነው፡፡ በበኩሌ የተቃዋሚው ጎራ በውህደትም ይሁን በሌላ መንገድ መጠናከሩን እፈልጋለሁ፡፡ የተቃውሞውን ጎራ የሚወክል አንድ ብቸኛ አውራ ፓርቲ እንዲኖር ግን አልሻል፡፡ ምንም ይሁን ምን የአንድ ጥሩ የለውም፡፡ ደግሞም አውራ ፓርቲነት ኢህአዴግ ሲለው ስህተት፣ ተቃዋሚው ጎራ ሲከጅለው ትክክል ሊሆን የሚችልበት አግባብ አይታየኝም፡፡ እንዲህ ያለው አካሄድ ፈረንጆቹ "Double Standard" የሚሉት ነውና መታረም አለበት፡፡

በውህደት ዙሪያ አንዲት ነጥብ ልጨምር፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት፤ የተቃዋሚውን ጎራ መጠናከር በተመለከተ ከአቶ አበበ ልዩነት የለኝም፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንዳች ተዓምር ካልተፈጠረ በስተቀር አሁን የተቃውሞውን ጎራ የሚመሩት የፖለቲካ ልሂቃን ከልብ የመነጨ ውህደት የመፍጠር ተፈጥሯዊ ባህሪ የላቸውም ብዬ ያለምንም ጥርጥር መናገር እችላለሁ፡፡ ይሄ ደግሞ አቶ አበበ እንደሚሉት ጨለምተኛነት አይደለም፡፡ ሁሉንም ነገር በውስጡ ሆኜ አስራ ሁለት ዓመታት ስላየሁት ጠንቅቄ አውቀዋለሁ፡፡ ለዚህም ነው ሀቀኛ ውህደት መፍጠር የማይችልን ኃይል እንዲዋሃድ ከመድከም (ተዋህዶ ሳያበቃ ለሚፈርስ ነገር) በተባበረ ኃይል አዲስ ፓርቲ ማቋቋም

ይሻላል የሚል አቋም መያዝን የመረጥኩት፡፡ ታላቁ የሩሲያ ደራሲ ኒኮላይ ጎጎል “ካፖርቱ” በሚል ርእስ የጻፈው ታሪክ የሚያስተምረን አሮጌ ቡትቶ ሲጥፉ ከመኖር አዲስ (ኦርጂናሌ) ማሰናዳት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

አቶ አበበ ይህንን ‘አዲስ ፓርቲ ይቋቋም’ የሚል ሃሳቤን “ከፖለቲካ ሳይንስ ምሩቅ የሚጠበቅ አደለም” ይሉታል፡፡ አለፍ ብለው በመሄድም “የፖለቲካ ቁማር ነው” ይሉኛል፡፡ የፖለቲካ ቁማር የሚሆነው እኔ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳትፎ ቢኖረኝና የፖለቲካ ትርፍ የማገኝበት ቢሆን ነበር፡፡ እኔ ፖለቲከኛ አደለሁም፡፡ ተራ ዜጋ ነኝ፡፡ በዚህ ወቅት የምደግፈውም ሆነ የምቃወመውም አይዲዮሎጂ የለኝም፡፡ እንደ ዜጋ “እንመራሃለን” የሚሉኝን ፖለቲከኞች “በወጉ ሁናችሁ ምሩኝ” ከማለት የዘለለ ፍላጎት የለኝም፡፡ እንደ ፖለቲካ ሣይንስ ተማሪነቴ አሁንም የምመክረው አዲሱ ትውልድ ድሪቶ አይጥቀም፡፡ ራሱ የሚመራው አዲስ ፓርቲ ያቋቁም ነው የምል! ለማንኛውም፤ ሀሳባችንን በዚህ መልኩ ከገለጽን በኋላ፣ ሁላችንም የየራሳችንን አቋም እንያዝ፡፡ የቁም ቅዠቱ የቱ እንደሆነ ጊዜ መልስ ይሰጠናል፡፡

‘በአንጋፋ ፖለቲከኞቹ’ ላይ ‘የከፋ ጥላቻ’ እንዳለኝም አቶ አበበ በጽሁፋቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ በበኩሌ በምድር ላይ አንድም የምጠላው ሰው የለም፡፡ እኔ የምጠላው የሰዎችን መጥፎ አስተሳሰብና ከመጥፎ አስተሳሰባቸው የሚመነጨውን መጥፎ ተግባራቸውን ብቻ ነው፡፡ እናም ሃሳቤን በሃሳብ ማቸነፍ ሲያቅትዎት “ጥላቻ፣ የፖለቲካ ቁማርተኛ፣...” ከማለት አልፈው “አቶ አብዱራህማን በምርጫ ዋዜማ ገዢውን ፓርቲ እንደ ሙሽራ አጅቦ ቤተመንግስት የሚያስገባ አዲስ ፓርቲ እንዲያቋቁሙ ለኢህአዴግ ልሂቃን ቃል...” ገብተዋል የሚል አስተያየት መሰንዘርዎ ተገቢ አደለም፡፡

ይህ አስተያየት በመጀመሪያ ደረጃ ቅንነት ይጎድለዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሎጂክ ይጎድለዋል፡፡ ከሎጂክ አኳያ ስናየው፤ አቶ አበበ በአንድ በኩል አዲስ ውህደት መፈጠር አለበት ይላሉ፡፡ አዲሱ የውህደት ውጤት አዲስ ስምና አዲስ አደረጃጀት ይዞ ነው እውን የሚሆነው፡፡ እኔ እንደምለው አዲስ ፓርቲም ቢቋቋም አዲስ ስምና አዲስ አደረጃጀት ይዞ ነው እውን የሚሆነው፡፡ ሁለቱም በምርጫ ዋዜማ ነው የሚከናወኑት፡፡ ታዲያ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ለውህደትም፣ ለአዲስ ፓርቲ ምስረታም ያለው ልፋት ያን ያህል የሰፋ ልዩነት ያለው አይመስለኝም፡፡ አቶ አበበ የኔ ሃሳብ ይበልጣል የሚሉ ከሆነ ተጨማሪ ማሳመኛ ያቅርቡ! እንዲሁ የእኔን ሃሳብ ያለ በቂ ምክንያት ማጣጣሉና የኢህአዴግ ተልእኮ ነው ማለቱ ከሎጂክ አኳያ ትርጉም የለውም፡፡

ወንድሜ አቶ አበበ! ምርጫው ገና አንድ ዓመት ተኩል ገደማ ይቀረዋል፡፡ ቅንጅት በምርጫ 97 ያን ሁሉ ተዓምር የሰራው በሰባት ወራት ነው፡፡ ‘አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ’ እንዲሉ በአጉል ይሉኝታ ተጠፍረን ማለባበሱ የትም አያደርሰንም፡፡ እንደማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ እየተማማሉና የጎሪጥ እየተያዩ ከመሄድ እየጎመዘዘንም ቢሆን ሀቁን መጎንጨት ነው የሚሻል፡፡ የኔ ስጋት በፖለቲከኞቹ ስህተት በሰላማዊ ትግል ላይ ህብረተሰቡን ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ እንዳይከሰት ነው፡፡

ሌላው አቶ አበበ መገንዘብ ያለባቸው ጉዳይ እኔም ኢትዮጵያዊ መሆኔን ነው፡፡ እንደ ዜጋ የሀገሬ ጉዳይ እኔንም ያገባኛል፣ ይመለከተኛል፡፡ እናም አሁንም ሆነ ወደፊት እንደ አስፈላጊነቱ ሃሳቤን የመግለጽም ሆነ የመከራከር መብት አለኝ፡፡ የማቀርበው ሃሳብ ይጥቀም አይጥቀም፣ ትክክል ይሁን አይሁን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ አቶ አበበ “አቶ አብዱራህማን በምርጫ ዋዜማ... አዲስ ፓርቲ እንዲያቋቁሙ ለኢህአዴግ ልሂቃን ቃል ገብተው...” ነው የሚሉት እኔን በማሸማቀቅ ሀሳቤን በነጻነት እንዳልገልጽ ለመገደብ ካልሆነ በስተቀር ከተራ አሉባልታነት የዘለለ ትርጉምም ፋይዳም

የለውም። እንዲያው ለነገሩ እርስዎን ኢህአዴግ ተልእኮ ሰጥቶዎት ነው እንዴ ጠንካራ፣ በአዲሱ ትውልድ የሚመራ አዲስ ፓርቲ አይቋቋም የሚሉት? የፍረጃና የሞቲቭ ፍለጋ መንገድ በሽታ ነው!

አቶ አበበ ራስዎን በማንም የማይመሩ፣ ለሀገርዎች ቅን አሳቢና የቁርጥ ቀን ልጅ አድርገው፤ እኔን ግን በራሴ የማልመራ፣ ኢህአዴግ የጫነኝን ተልእኮ ተሸክሜ የምጓዝ ጌኛ (አጋሰስ)፣ በሀገሬ ጉዳይ የማያገበኝ "ወያኔ" አድርገው ሲያቀርቡ ትንሽ ህፍረት አይሰማዎትም? እርስዎ "ወያኔ" ላለመሆንዎ ምን ማረጋገጫ ይዘዋ? እንዲህ ያለ "እኔ ጋ ካልሆንክ እነዚያ ጋ ነህ" የሚል የፍረጃ መንገድ ላለፉት ሃምሳና ስልሳ ዓመታት ታላላቆቻችን ሲሄዱበት የነበረ ውጤት አልባ መንገድ ነው። አቶ አበበ እኔና እርስዎ ይህንን የመሀል ሀገር ፖቲከኞችና ልሂቃን የውድቀት መንገድ መከተል የለብንም። ከእነርሱ የተሻልን መሆናችንን እነርሱ ያላደረጉትን በማድረግ እና እነርሱ ባልሄዱበት መንገድ በመሄድ ማሳየት ይኖርብናል የሚል እምነት አለኝ። እናም ከንግዲህ መከራከር ያለብን በሃሳብ ላይ መሆን አለበት እንጂ ካነሳነው ሃሳብ በስተጀርባ ይኖራል ብለን በምናስበው ነገር (Motive) ወይም በፍረጃ (labeling) ላይ መሆን የለበትም። አበቃሁ።